## ይኸን ያውቁ ኖሯልን !

ላለፉት አምስት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፈጣንና ተከታታይ እድገት እያስመዘገበ ይገኛል:: ከ1996-2000 ዓ/ም ባሉት አምስት አመታት ውስጥ በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ ዓመታዊ እድገት መታየቱ በአገራችን ታሪክ ተሰምቶ የማይታወቅ አዲስ ክስተት ነው:: ይኸንን ክስተት በማስመልከትም ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ጠበብትና ተንታኝ ወገኖች ኢትዮጵያ ከሰሃራ በረሃ በታች ካለት አገሮችና ባጠቃላይም ኢኮኖሚያቸው በነዳጅ ምርት ውጤት ላይ ከተንተራሰው አገሮች ውጭ በፈጣን እድገት ግሥጋሴዋ ከአፍሪካ አህጉር የቀዳሚነቱን ደረጃ መጨበጧን ያሰምሩበታል:: ይህ ብቻም አይደለም The African Rainbow Index በመባል የሚታወቀው የሀገሮች ምጣኔ ሀብት አጥኚ ተቋም በቅርቡ ባወጣው ዘገባው ኢትዮጵያ ከናይጄሪያ ቀጥሎ በአፍሪካ በኢንቨስትመንት መስህቧ ግንባር ቀደም ረድፍ ላይ መሰለፏን አረጋግጧል:: ለኢኮኖሚያችን እድገት ነፀብራቅና የእድገቱን ቀጣይነት ከሚወሰኑት ሁኔታዎች ውስጥም ጉልህ ድርሻ የሚይዘው በፋይናንስና በውጪ ንግድ ዘርፍ የግሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በኩል የተወሰደ የፓሊሲ እርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች ናቸው::

ከነዚህ የፓሊሲ እርምጃዎችና ውጤቶቻቸው መካከል የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መስፈን የባንኮችና የሌሎች የፋይናንስ ተቋማት በዓይነት፣ በጥራትና በብዛት እንዲያድጉ አመቺ ንፍቀ ክበብ እንዲኖር ማስቻልና በውጭ ንግድ ዘርፍ ረገድ ሌሎች አበረታች እርምጃዎች መውሰድ ይገኙባቸዋል:: እስቲ ለግንዛቤ እንዲረደ የፋይናንስ ተቋማት ዕድገት በተመለከተ በዚህ ጽሁፍ ጀርባ ያለውን ሠንጠረዥ ለእይታ ይቃኙ፣

እዚህ ላይ ልዩ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ መንግሥት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲችሉ የነደፋቸው አመቺ የፖሊሲ መደላድሎች ጠቃሚ ውጤት ማስመዝገብ መጀመራቸው ነው::

## *የፋይናንስ ተቋማት እድገት*

| ቁጥር | | 1984 በጀት ዓመት | 2000 በጀት ዓመት |
|---|---|---|---|
| 1 | የባንኮች ቁጥር | 3 | 12 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 3 | 3 |
| | የግል ባንኮት | | 10 |
| 2 | የባንኮች ቅርንጫፍ ብዛት | 194 | 562 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 194 | 264 |
| | የግል ባንኮች | 0 | 200 |
| 3 | የባንኮች ጠቅላላ ሀብት/ ሚሊዮን ብር/ | 9,484.6 | 113,603.3 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 9, 484.6 | 78,022.8 |
| | የግል ባንኮች | - | 35,580.5 |
| 4 | የተቀማጭ ገንዘብ ክምችት | 5,898.2 | 62.956.3 |
| | የመንግሥት ባኮች | 5,898.2 | 40,765.7 |
| | የግል ባንኮች | - | 22,190.6 |
| 5 | የብድር ገንዘብ ክምችት /በሚሊዮን ብር/ | 4,167.9 | 41,339.8 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 4,167.9 | 24,894.9 |
| | የግል ባንኮች | - | 16,444.9 |
| 6 | የባንኮች ካፒታል /በሚሊዮን ብር/ | 1,352.7 | 9,965.0 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 1,352.7 | 6,601.0 |
| | የግል ባንኮች | - | 3,364.0 |
| 7 | የኢንሹራንስ ኩባንያዎች | 1 | 10 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 1 | 1 |
| | የግል ባንኮች | 0 | 9 |
| 8 | የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ቅርንጫፍ ብዛት | **20** | **172** |
| | የመንግሥት ባንኮች | 20 | 37 |
| | የግል ባንኮች | - | 135 |
| 9 | የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ካፒታል /በሚሊዮን ብር/ | 11 | 582.1 |
| | የመንግሥት ባንኮች | 11 | 229.3 |
| | የግል ባንኮች | - | 352.8 |

## ታዲያስ የርስዎ ሚና ምን ይሁን?

በሀገራችን የኢንቨስትመንት አውድማ ያለንን ጥሪት በማፍሰስ ራሳችንና ወገናችንን ለመጠቅም ርብርብ ማድረግ በተለይም እኛ የዲያስፖራው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የመዋዕለ ንዋያችንን እውቀትና ክሂሎቶችንን የርስ በርስ ግንኙነታችንና እንዲሁም ከምንገኝበት አካባቢ የፈጠርነውን ትስስር በማቀናጀት ለሀገር ልማት፣ ለወገን ተገን፣ ለራስ ለራሳችንና ለቤተሶቦቻችን ትሩፋት የምንሸምትበት አጋጣሚ ዛሬ ነው።

ለተሳትፎ! አቶ ፈቃዱ በየነ / አማካሪ/
ስልክ ቁጥር 202 364 6388 fekadu@ethiopianembassy.org
Embassy of Ethiopia
3506 International Dr. NW
Washington DC. 20008